# መንጋቱ ታወቀኝ

ማለዳ ወፎቹ ሲንጫጩ...
እኔ አንቀላፋለሁ እኔ ተኝቻለሁ
መንጋቱን ረስቼ ህልሜን አልማለሁ
አሁንም ተንጫጩ...
ተነሽ ተነሽ አሉኝ ውስጥሽን እወቂው
ሌላውን አትሁኝ ራስሽን ፈልጊው
ጆሮዬ እየሰማ አይኔም ሁሉን አይቶ
አላየሁም አልኩኝ አልሰማሁም ከቶ
እኔ ላይ ተኝቼ ሌላ አልማለሁ
ማንነቴን ክጄ ሌላውን ሆኛለሁ
ጫጫታው ሳያቆም ጥሪው ሳያበቃ
ድንገት ብንን ስል ከእንቅልፌ ስነቃ
የተማመንኩበት የካብኩት ተንዶ
እንዳልነበር ሆናል ውስጤም ሆኖል ባዶ
ያ..የወፎች ጩህት አሁንም ቢጠራኝ
ህልሜንም ረገምኩት ምኞቴን ታዘብኩኝ
ራሴን ትቼ ሌላን መሁኔም አስቆጨኝ
በከንቱ ያሳለፍኩት አሁን ውስጤን በላኝ
የወፎቹ ጩህት ጥሪያቸውም ገባኝ
ጊዜው መገስገሱ መንጋቱ ታወቀኝ::

ዙበይዳ አወል (1988 /1995)